# *ዜጎችን ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ የማባረር ሂደት ህገመንግስታዊ አንደምታ እና ትዉፊታዊ እሴቱ*

*በሸንቁጥ አየለ (shenkutayele@yahoo.com )*

*በዘራቸዉ አማሮች የሆኑ አርሶ አደር ዜጎች ከቤንች ማጅ ዞን ከጉራ ፋርዳ ወረዳ ሀብት ካፈሩበት ፤ በህጋዊነት መሬት ይዘዉ እየገበሩ እያረሱ ከኖሩበት ቀያቸዉ አገራችሁ አይደለም፤ ደን ጨፍጭፋችሁዋል፤ ሀብታም እየሆናችሁ ባካባቢዉ ነዋሪ ላይ ተፅዕኖ ፈጥራችሁዋል በሚሉ ሰበቦች እንዲባረሩ እየተደረጉ መሆኑን ልዩ ልዩ ሚዲያዎች በሰፋትና በጥልቀት እየዘገቡት ይገኛሉ፡፡ የአሜሪካ ድምፅ፤ ጀርመን ድምፅ ፤ ሪፖርተር ጋዜጣ፤ አዲስ አድማስ ጋዜጣ፤ ፍትህ ጋዜጣና ልሎችም ሚዲያዎች የተፈናቀሉ ሰዎችን ጭምር እያቀረቡ ነገሩን በሰፋት ለህዝብ አቅርበዉ ህዝብም በጉዳዩ ላይ መያዬት ከጀመረ ሰነባበተ፡፡*

*ስለተባረሩ ሰዎች ክልሉ በመገናኛ ብዙሃን የተለያዩና የሚቃረኑ መግለጫዎችን ሲሰጥ ይሰማል ፡፡ የፌደራል መንግስትም በጉዳዩ ላይ ያለዉን አቋዋም ግልፅ አድርጎ አስቀምጦአል፡፡ ከመንግስት ወገንም ሆነ ከተለያዩ አካላት ድርጊቱን በመደገፍና በመቃወም የተለያዩ መግለጫዎች ቢሰጡም የህገ መንግስቱ የባለስልጣናትን ሰነ ባህሪና ድርጊት ገዥነት ብሎም የዉሳኔያቸዉ ብቸኛ መሰረት ሊሆን እንደሚገባዉ በጥልቀትና በሰፋት ሲተነተን አይስተዋልም፡፡ የዜጎች ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ የመባረር ጉዳይ መሰፈርና መለካት ያለበት ሀገሪቱ ካላት ህገመንግስት ማዕቀፍ አንፃር ብቻ እንጅ ፖለቲከኞች፤ ባለስልጣኖች ወይም ተቃዋሚዎች ከሚሰጡት ትንታኔ አንፃር ሊሆን አይገባም፡፡ ስለዚህ የዚህ ፅሁፍ ዋና አላማ ይህ ድርጊት ከህገ መንግስቱ አንፃር ምን አንደምታ አለዉ ? ለመፃኢቱ ኢትዮጵያስ ምን ትዉፊታዊ እሴት ሊያወርስ ይችላል? የሚሉት ነጥቦችን በተወሰነ ደረጃ ለመዳሰስ መሞከር ነዉ፡፡*

## 1. በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የመኖር መብት

*በህገ መንግስቱ መሰረት ወላጆቹ ወይም ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነዉ (አንቀፅ 6/1) ፡፡ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደግሞ በህገ መንግስቱ የተቀዳጃቸዉ መብቶች አሉት፡፡ እነሱም በህግ ይጠበቁለታል፡፡ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ከፈቃዱ ዉጭ ዜግነቱ ሊገፈፍ አይችልም (አንቀጽ 33/1 )፡፡ ደግሞም ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት የሚያስገኘዉን መብት፤ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለዉ (አንቀጽ 33/2).፡፡ ህገ መንግስቱ ለማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመዘዋወር ነፃነት በአንቀፅ 32 አጎናፅፎአል፡፡ ወላይታ ፤ ሲዳማ ፤ አማራ ፤ኦሮሞ ፤ ሶማሊ፤ ሐረሪ ፤ ትግሬ ወይም ሌላ ብሄር ሳይጠቅስ ስለ መዘዋወር ነፃነት እንዲህ ይላል፡-ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወይም በህጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ዉስጥ የሚገኝ የዉጭ ዜጋ በመረጠዉ የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖርያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገዉ ጊዜ ከሀገር የመዉጣት ነፃነት አለዉ ፡፡ ሆኖም የደቡብ ክልል መንግስት ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች ከክልሉ እንዲባረሩ በደብዳቤ ሲያዝ ከላይ የተጠቀሱ ህገ መንግስታዊ አንቀፆችን ያገናዘባቸዉ አይመስልም፡፡ አንድ ሰዉ ከኢትዮጵያ ከየትኛዉም አቅጣጫ ቢመጣም በአንድ የክልል ሀላፊ በተሰጠ የደብዳቤ ትዕዛዝ የዜግነት ህገመንግስታዊ መብቱ ሊጣስ አይገባም፡፡*

*ደግሞም የክልሉ ፖለቲከኞች ሲናገሩ እንደሚደመጠዉ ክልሉ ያባረራቸዉ ህገ ወጥ የሆኑትን ከሰሜን አማራ የመጡ ዜጎችን ነዉ፡፡ለምሆኑ አንድ ዜጋ ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ሲንቀሳቀስ ህዊ ያልሆነ ዜጋ ሊያስብለዉና ከዚያ ክልል እንዲባረር የሚያስደርገዉ ምን ህገ መንግስታዊ አንቀፅ አለ ? ህገ መንግስቱ የዜጎችን የመዘዋወርና መኖሪያን እና ስራን የመምረጥ መብትን አረጋግጦአል፡፡ አንድ ዜጋ ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ሲሄድ የክልሉን እና የአካባቢዉን አሰፈላጊ ህጎች እንዲያሙዋላ ይጠዬቃል እንጅ ከሌላ አካባቢ መጣህ ተብሎ ከአካባቢዉ አይባረርም፡፡ ምንም እንኩዋን ክልሉ ህጋዊነት የሌላቸዉን አባረርሁ ብሎ ቢናገርም የተባረሩት ዜጎች ደግሞ ግብር የገበሩበትን ካርኒ ሁሉ ሲያቀርቡ ተስተዉለዋል፡፡ ሆኖም ዋናዉ ጥያቄ አንድ ክልል ከሌላ ክልል የመጣ ኢትዮጵያዊ ዜጋን የማባረር ህገ መንግስታዊ ስልጣን አለዉ ወይ ? የሚለዉ ጉዳይ ነዉ ፡፡*

## *2. የዜጎች ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች*

*የማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች ሊከበሩለት እንደሚገባ በህገ መንግስቱ በአንቀፅ **43** ስር እንዲህ ሲል ተብራርቶአል፡-*

- *ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ዉስጥ በማንኛዉም ኢኮኖሚዊያ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ስራ የመስራት መብት አለዉ **(43/1)***
- *ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያዉን ስራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ **(43/2)***
- *መንግስት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ስራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል **(43/6)***
- *መንግስት ዜጎች ጠቃሚ ስራ የማግኘት ዕድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል **(43/7)***
- *ገበሬዎችና ዘላን ኢትዮጵያዉያን በየጊዜዉ እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸዉና ለምርት ካደረጉት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ዉጤቶቻቸዉ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡ መንግስት የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ መርህ መመራት አለበት **(43/8)***

*ሆኖም ይህን የመሰለዉ ዉብ የህገመንግስት ክፍል ጉራ ፋርዳን አገራችን ብለዉ በአካባቢዉ ለብዙ ጊዜ ሰፍረዉ ይኖሩ እነበሩ ዜጎች ጋ ሲደርስ ከፉኛ ተጥሶአል፡፡ ግብርና ሙያን መርጠዉ ፤ በጥረታቸዉና በጉልበታቸዉ ድህነትን አሸንፈዉ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በትጋት እየተሳተፉ ያሉ ዜጎችን ለማፈናቀል ከተሰጡ ምክንያቶች አንዱ ሀብታም እየሆናችሁ በአካባቢዉ ማህበረሰብ ላይ ጫና ታመጣላችሁ የሚል ነዉ፡፡ እናም አማሮቹ ገበሬዎች ይህ ህገ መንግስታዊነት ቀርቶ የልማት ፅንሰ ሀሳብ ሊገልፀዉ በማይችል ህሳቤና ሰበብ ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ ይባረራሉ፡፡*

*የክልሉ መንግስት በአንቀፅ **43/8** እንደተደነገገዉ እነዚህን አርሶ አደሮች ሊያበረታታ እና ኑሮአቸዉም እንዲሻሻል ማገዝ ሲገባዉ ከቤታቸዉ ገፍትሮ በማስወጣት ያፈሩትን ሀብት እንኳዋን በቅጡ ለማደራጀት ጊዜ ሳይሰጣቸዉ አስገድዶ ያባርራቸዋል፡፡ ይህን ጉዳይ ሪፖርተር ጋዜጣ፤ አዲስ አድማስ ጋዜጣ፤ ፍትህ ጋዜጣ በስፋት የዘገቡት ሲሆን የዉጭ ሚዲያዎች የነገሩን ክብደት አፍታትተዉና አብራርተዉ ለማቅረብ የተፈናቃዮችን ምስክርነት እያጣቀሱ አቅርበዉታል፡፡ ጉዳዩን **ወገቡን ጠበቅ አድርጎና** በቅርበት የሚከታተለዉ፤ ለተፈናቃዮችም መጠለያ በመስጠት፤ የተለያዩ የተቃዉሞ መግለጫዎችን በማዉጣት፤ለጠቅላይ ሚኒስትሩም የተቃዉሞና የተማፅኖ ደብዳቤ በመፃፍ የሰዎች መባረር እንዲቆም የጠዬቀዉ ብሎም ግንባር ቀደሙን ሀገራዊ ሚና እየተወጣ ያለዉ ተቃዋሚዉ የፖለቲካ ፓርቲ የሆነዉ መኢአድ ደግሞ በቢሮዉ ለተፈናቃዮች መጠለያ ከመስጠት እስከ ምግብ ማቅረብ ተራምዶ **ብዙ መቶዎች የሚሆኑ** ተፈናቃይ ገበሬዎችን በቻለዉ ሁሉ ለመርዳት ሲረባረብ ተስተዉሉዋል፡፡*

*ለምሆኑ በጥረታቸዉ ሀብት ያፈሩ ሰዎችን ፤ የዜግነት መብታቸዉን ተጠቅመዉ በሀገሪቱ ተዘዋዉረዉ ግብርናን ስራ አድርገዉ በመምረጥ በግብርና ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ከሀገራቸዉ ማባረር ነዉ የሚገባዉ ወይስ በኢኮኖሚ እንዲጎለብቱ ፤ በባህል እንዲጠናከሩ በልዩልዩ ፖሊሲዎች መደገፍ ነዉ ተገቢዉ ህገ መንግስታዊ ትዕዛዝ? ዜጎች በመረጡት አካባቢ ለመኖር እና በመረጡት ስራ ለመተዳደር ተዘዋዉረዉም የተሻላቸዉን አካባቢ መርጠዉ መኖር መጀመራቸዉ ህጋዊ አካሄድ መሆኑን የክልሉ መንግስት ለምንድነዉ የማይቀበለዉ?*

*ክልሉ የሚሰጣቸዉ ምክንያቶች በሙሉ በህገ መንግስቱ መነፅር ሲቃኙ የዜጎችን ህገ መንግስታዊ መብት □ሚንዱ እንጂ በምንም መልኩ ህገ መንግስታዊ መሰረት የላቸዉም፡፡ እንደሚታወቀዉ ህገ መንግስቱ የህጎች ሁሉ የበላይ (አንቀፅ 9/1) መሆኑ ቢታወጅም ይህ ህገመንግስት አሁን እተፈናቀሉት ሰዎች ላይ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቶአል፡፡ ከሰሜን አማራ የመጡ ዜጎች ደቡብ ኢትዮጵያን ስለተቆጣጠሩት ወደ መጡበት እንመልሳቸዉ ማለት ከላይ ያዬንዉን የዜግነት መብት መንጠቅ ስለሆነ ህገ መንግስቱንም መናድ ነዉ፡፡ ለምሆኑ ክልሉ ከህገ መንግስቱ በላይ የሆነ ተጠይቅና ህግ መፍጠር ይችላል ወይ ? ወይስ ህግ አስፈፃሚዊ የመንግስት አካል በመሰለዉና*

*ያዋጣኛል ባለዉ መልክ ብድግ እያለ ህገ መንግስቱ ዉስጥ የቆሙ መሰረታዊ የህግ መርሆችን ሳያገናዝብ የራሱን አስተዳደራዊ ትንታኔዎች መስጠት ይችላል ወይ?*

*ዛፍ ሲመነጥሩ ስለተገኙ ተባረሩ የሚለዉ ሰበብ በህገመንግስቱ ዉስጥ ከተዘረዘሩት የዜጎች መብት ጋር ሊሄድ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች ዛፍ ሲመነጥሩ ብሎ መናገር ምን ማለት ነዉ? አማራ ስለሆኑ ዛፍ ምንጠራ ይወዳሉ ማለት ነዉ? ነዉ ወይስ ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ ገበሬ የተለዩ የዛፍ አጥፊነት ባህሪ አላቸዉ ማለት ነዉ? ነዉ ወይስ የአማራ ገበሬዎች እንደ እብድ ዛፍ የማዉደም ሰነል ልቦና አላቸዉ ማለት ነዉ? ደግሞስ በሽህ የሚቆጠሩ ሰዎች በህብረት ተመካክረዉ ዛፍ ምንጠራ ላይ ይሳተፋሉ ማለት ነዉ?*

*ምናልባትም ከመሃላቸዉ ጥፋተኛ ከተገኘ በአካባቢዉ ህግ እንደማንኛዉም አርሶ አደር ፍርድቤት ቀርቦ መቀጣትና መታረም እናዳለበት እሙን ነዉ ፡፡ ሆኖም ከሰሜን አማራ የመጣ ዜጋ ስለሆነና ዛፍ ሲመነጥር ስለተገኘ ወደ ሰሜን አማራ መልሱት ማለት የዜጎችን ህገመንግስታዊ መብት መጣስ ነዉ፡፡*

*ህገ መንግስቱም ለአካባቢ ጥበቃ ህጋዊ አካሄዶችን እንደሚከተለዉ በአንቀፅ **92** አስቀምጦአል፤-*

- *መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖር የመጣር ሀላፊነት አለበት **(92/1)***
- *የህዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ስራ ላይ በሚዉልበት ጊዜ የሚመለከተዉ ህዝብ ሁሉ ሀሳቡን እንዲገልፅ መደረግ አለበት **(92/3)***
- *መንግስትና ዜጎችች አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸዉ**(92/4)***

*እንግዲህ ህገ መንግስቱ አንድ የተረዳዉ ነገር አለ፡፡ የማህበረሰብና የዜጎች ተሳትፎ በሚወጡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ወሳኝ መሆኑን፡፡ ይህም ማለት የህዝቡ ተሳትፎ ከሌለ በማህበረሰቡ ዘንድ ስለሚወጡ ፖሊሲዎች የግንዛቤ ዝቅተኝነት ሊኖር ስለሚችል ማህበረሰቡን በፖሊሲ ቀረጻ ላይ በማሳተፍ ፕሮጋራሞችን የራሱ እንዲያደርጋቸዉና አካባቢዉን የመንከባከብ ግዴታም እንዳለበት እንዲረዳ የማድረግ ስራ መሰራት እንዳለበት ያስረዳል ፤ የህጎች የበላይም ነዉና ያዛል፡፡*

*ይህ አስተሳሰብ ደግሞ በተሳትፎአዊ የልማት ሳይንስም ተቀባይነት ያገኘ አስተሳሰብ ነዉ፡፡ በሁሉ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ቀረፃ ላይ ህዝቡ ይሳተፍ የሚለዉ የዘመናችን ቁልፍ መርህ እሆነ መጥቶዋል፡፡ ያን ጊዜም ህዝብ የሚከናወኑ ልማቶችን እና ስራዎችን የራሱ የማድረግና በአካባቢም ሆነ በልማት ስራዎች ላይ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ጥፋትን እንዳያመጣ ይሆናል፡፡*

*ሆኖም ዜጎች አንድ ጠፋት ሲያጠፉ ማባረር ያዉም ከሰሜን አማራ የመጡ በሚል ሀሳቤ ተነሳስቶ አባር የሚል አንደምታና ታሳቢን በህገ መንግስቱ ዉስጥ አንድም ቦታ የለም፡፡ ለአማሮቹ አርሶ አደሮች ቤቶች ማጂ ከአካቢዉ ነዋሪዎች እኩል አገራቸዉ ስላልሆነ ደን ሲያወድሙና ዛፍ ሲቆርጡ ስለተገኙ ወደ መጡበት ይመለሱ የሚለዉ አስተሳሰብና ትንታኔ የሀገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ በሆነዉ ህገ መንግስት አንድም ተደጋፊነት የለዉም፡፡ አገራችን ደቡብ ኢትዮጵያም፤ ኦሮሚያም ትግራይም ፤ሶማሊያ ክልልም፤ አፋርም ፤ ጋምቤላም ነዉ ብለዉ ለሚያምኑ ዜጎች ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች በሚል ሀሳቤ በሀይል ወደ ክልላቸዉ ማባረር ተገቢ ነዉ የሚል ሀሳቤን የቋዋጠረ ህገ መንግስታዊ ሰንኝ አንድም ቦታ የለም፡፡*

*ደግሞም ይህ አይነት አስተሳሰብ በህገ መንግስቱ ከተደነገጉ ህጎች በላይ ጎልቶ ከወጣ በበርካታ ኢትዮጵያዉን ላይ ምን አይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል የሚለዉን ጣጣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዉል የሚረዳዉ ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ብቸኛዉ የፓርላማ ተመራጭ የሆኑ ከቡር አቶ ግርማ ሰይፉ የሰዎቹን መባረር አስመልክተዉ ጥያቄ ሲጠይቁ የሚከተለዉን ጥልቅና የተሰደረ ሀሳብን ለመላዉ ኢትዮጵያዊ ባለአዕምሮ ሁሉ አካፍለዋል ' እንደሚታወቀዉ ክልላቸዉ አዲስ አበባ ባይሆንም በርካታ ኢትዮጵያዉያን በአዲስ አባባ እየኖሩና ኢንቨስት እያደረጉ ነዉ፡፡ ወደፊትም በርካቶች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፡፡ እና አዲስ አበባ የእኔ ነዉ የሚል ወገን ድንገት ብድግ ብሎ ወደ*

*ክልላችሁ ወጡ ቢልስ?' የእኝህን ሰዉ ጥያቄ በነፃ ልቦና ብሎም በአርቆ አስተዋይ ህሊናዉ የመረመረ ባለአዕምሮ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደግሞ ጥያቄያቸዉን ሰፋ አድርጎ በህሊናዉ ነገ የራሱን እጣ ፋንታ እያሰላሰለ ለምሆኑ ዛሬ በአማሮቹ ላይ የደረሰዉ ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ አማራ ክልል መባረር ምን አይነት የትዉልድ ትዉፊታዊ እሴትን ያወርሰን ይሆን እያለ በሀሳብ ሳይናጥ አይቀርም፡፡ ማህበረሰብ የማይናጥና የማይናወጥ የህግ መሰረት ላይ ቆሞ እጣፋንታዉን በግልፅ የህግ መርሆዎች መዳኘት እስካልቻለ ድረስ እዉነትም በሃሳብ መናጡ መቆሚያ የሚኖረዉ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሌላዉ ቀርቶ ዛሬ እጁ ላይ ጉልበትና ሀይል ተባብረዉ የገቡለት ወገን እንኳዋን በተሰደረ የህግ መሰረት ላይ ስለመቆሙ እርግጠኛ ካልሆነ በሰመመን መናጡና መናወጡ አይቀርም፡፡ የህግ ፈላሰዉ ጆን ሎክ እንደሚለዉ ማህበረሰብ በህግ ማዕቀፍ ስነባህሪዉና ድርጊቱ ካልተመራና ካልተገዛ የአራዊት ባህሪ አለዉ፡፡*

*ዜጎች በግዳጅ ከአገራቸዉ ኢትዮጵያ ወደ ሌላዉ የኢትዮጵያ ክፍል ክልላችሁ ካልሆነዉ ክልላችሁ ወደ ሆነዉ ተብለዉ ሲገፈተሩ የሚኖረዉን ጫና ፤ የስነልቦና ቀዉስ ፤ የንብረት ብክነት እና ተያያዥ ጉዳዮችን በንፁህ ልቦናዉ እያሰበ የሚደመም የአዳም ልጅ በህሊናዉ የሚርመሰመስበት መሰረታዊ ተጠይቅ የጆን ሎክ ሀሳቡን እየፈተሸ በመቀመጫዉ ላይ ቁልቁል በሚያስጥም ጥቁር ራዕይ ከመጻኢዉ ትዉልዱ ጋር እያወጋ መባተት ብቻ ነዉ፡፡*

*ዜጎች ቤንች ማጂ ዞን መኖሪያ ፍሊጋ ያቀኑት ወይም በቤንች ማጅ ኖረዉ ሀብት ያፈሩት ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸዉን ተመርኩዘዉ እንዲሁም መንግስት የሚባለዉን ተቋም ታምነዉ ነዉ፡፡ መንግስት ደግሞ በህገ መንግስቱ በአንቀፅ **89** እንደተገለፀዉ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ እርምጃቸዉን የመደገፍ ግዴታ አለበት፡-*

- *መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱ የተጠራቀመ እዉቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀዬስ ሀላፊነት አለበት **(89/1)***
- *መንግስት መሬትን እና የተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በይዞታዉ ስር በማድረግ ለህዝቡ ጥቅምና እድገት እንዲዉሉ ማድረግ አለበት**(89/5)***

*የፌደራል መንግስት በግልፅ እንዳመነዉ በአካባቢዉ ሊኖር ለፈለገ ዜጋ ብቁ የሚሆን ባዶና ሰፊ ስፈራ በጉራ ፋርዳ ወረዳ አለ፡፡ ምናልባትም ዜጎች ህገመንግስታዊ መብታቸዉን ተጠቅመዉ ወደ አካባቢዉ መኖሪያ ፍሊጋ የሚሄዱት በተናጠል፤ ለልማት በማይመችና ባልተደራጀ ሁኔታ እንኳዋን ቢሆን መንግስት ማድረግ ያለበት ሁኔታዎችን ለዜጎች ማመቻቸትና ዜጎችም የሚሰጣቸዉን መመሪያ ተከትለዉ በተሻለ ሁኔታ እንዲሰፍሩ አቅጣጫ ማሲያዝ እንጅ ህገ መንግስታዊ መብታቸዉን ጥሶ ወደ መጣቸውሁበት ጥፉልኝ ማለት ህገ መንግስቱን መናድ ነዉ፡፡*

*ህገ መንግስቱ በየትኛዉም የሀገሪቱ ክፍል በሚገኝ ሀብት ለመበልጸግና ለመጠቀም ለዜጎች ሁሉ ፈቅዶ ሳለ የአንድ ክልል ሰዎች ወደ አንድ አካባቢ ሲሄዱ አንዴ ሀብታም ሆነዉ በአካባቢዉ ነዋሪ ላይ ተፅዕኖ አመጡ ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ደን ጨፈጨፉ ስለዚህም ወደ ሰሜን አማራ ይመለሱ ማለት አንድም ህገመንግስታዊ መሰረት የሌለዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡ ደግሞስ ክልሉ የዜጎችን ህገ መንግስትዊ መብት ገፎ ሰዎቹ በአካባቢዉ እንዳይኖሩ የሚያባርራቸዉ በምን ስልጣኑ ነዉ?*

### *3. በብሄር ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት*

*የተለያዩ ሚዲያዎችና በድርጊቱ ላይ ተቃዉሞአቸዉን ያሰሙ አካላት ተበዳዮችን እየጠዬቁና እያነጋገሩ ሁኔታዉን እንዳቀረቡት እነዚህ ተፈናቃዮች መብታቸዉን ለመጠዬቅ ወደ ተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናትና ልዩ ልዩ ፍርድ ቤቶች ሲንከራተቱ የገጠማቸዉ ሁኔታ እጅግ ዉስብስብ እንደሆነ ተብራርቶ ቀርቦአል፡፡ እንዲያዉም የእስር፤ የማስፈራራት እና የማጉላላት ዕጣ ፋንታ ሁሉ ደረሰብን የሚለዉን እሮሮአቸዉን የአሜሪካ ድምፅ ፤ የጀርመን ድምፅ ፤ የተለያዩ ነፃና ገለልተኛ የግል ሚዲያዎች እንዲሁም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሰፋት አቅርበዉታል፡፡ ህገ መንግስቱ ግን እንዲህ ይላል፤- ማንኛዉም ሰዉ ሰበዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለዉ (አንቀፅ **14**)፡፡ ማንኛዉም ሰዉ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለዉ(አንቀፅ*

*16)፡፡ በህግ ከተደነገገዉ ስርዓት ዉጭ ማንኛዉም ሰዉ ወንድም ሆነ ሴት ነፃነቱን አያጣም(17/1)፡፡ ማንኛዉም ሰዉ በህግ ከተደነገገዉ ዉጭ ሊያዝ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም (17/2)፡፡*

*ሆኖም እነዚህ ሁሉ ህጎች ተጥሰዉ አላግባብ መታሰር ፣ድብደባ ፣ ወከባ ፣ ንብረት ማቃጠል እና ከሀገራቸዉ መባረር ሲገጥማቸዉ ይህን ህገ መንግስት ለማስጠበቅ የቆመ ሀይል ሁሉ ለምን በርቀት ቆሞ ያስተዉላል ? ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች የሚለዉ ትንታኔስ በዉስጡ ምን ይዞአል?*

*በክልሉ ባለስልጣናት የሚሰጠዉ መግለጫ የዘር ጉዳይ እንዳለበት በግልፅ የሚያመላክት ሆኖ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የደቡብ ክልል ዋና ሀላፊ ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች ሲሉ ያስተላለፉት ትዕዛዝ ይሄንኑ የዘር ጉዳይ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ህገ መንግስቱ ምንም አይነት መድሎና መገለል ዘርን መሰረት አድርጎ ሊደረግ እንደማይገባ እንዲህ ያብራራል፡- ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸዉ፡፡ በመካከላቸዉ ማንኛዉም ዓይነት ልዩነት ሳደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር በብሄር በብሄረሰብ በቀለም በፆታ በቋንቋ በሀይማኖት በፖለቲካ በማህበራዊ አመጣጥ በሀብት በትዉልድ ወይም በሌላ አቋዋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ (አንቀፅ 25) .*

*ደግሞም አንድ አካል ከህገ መንግስቱ ወይም ከህጎች አንዱን ጥሶ ቢገኝ ማናኛዉም ሀላፊና የህዝብ ተመራጭ ሀላፊነቱን ሲያጎድል ተጠያቂ ይሆናል (አንቀፅ 12/2) ፡፡ እንዲሁም የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልፅ በሆነ ሁኔታ መከናወን አለበት (አንቀፅ 12/1) ፡፡ እናም ዜጎች ሲበደሉ ፣ህግ አለ አግባብ ሲፈርስና ሲናድ አፋጣኝ እርምጃ መዉሰድ ተገቢ ሆኖ ሳለ ሁሉም አካላት ነገሩን እንዳላዩ አይተዉ ያለፉት ስለምን ይሆን?*

*በህገ መንግስቱ በአንቀፅ 18 ኢሰበአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ አንዲህ ይላል ፡-ማንኛዉም ሰዉ ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰበአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለዉ (18/1)፡፡ ሆኖም ከቤንች ማጅ እየተባረሩ ያሉ አማሮች ይህ ሁሉ ህገመንግስታዊ መብታቸዉ መጣሱን ልዩ ልዩ ሚዲያዎች እራሳቸዉ ተበዳዮቹን እያጣቀሱ አቅርበዋል፡፡ ለምሳሌም አንዱን አርሶ አደር ከአካባቢዉ እንዲለቅ ሲጠዬቅ ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት ሲዘዋወር ስለተገኘ በዱላ ተቀጥቅጦ በደረሰበት ድብደባም አቀሉን ስቶ ከመኪና ላይ ወድቆ መሞቱን የአሜሪካን ድምፅ የተበዳይ ቤተሰቦችን እያነጋገረ ዜናዉን አቅርቦአል፡፡*

*ኢትዮጵያ በርካታ አለም አቀፍ የሰበአዊ መብቶችንና ስምምነቶችን ተቀብላ በህገ መንግስት አፅድቃቸዋለች፡፡ ከእነዚህ ስምምነቶች ዉስጥ አንዱ ዜጎች በኑሮአቸዉ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ድረጊት ተፈፅሞባቸዉ ቢገኝ እንደ ዘር ማጥፋት ወንጀል የሚወሰደዉ ነዉ የሚለዉ ህግ ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም በሰብእና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች በህገ መንግስቱ በአንቀፅ 28 ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ እንደሚደረጉ ያትታል፡፡ ሆኖም ይህ ሁሉ ህግና አንቀፅ እያለ እነዚህ ዜጎች ለምን መብታቸዉ ይሄን ያህል ተጣሰ? በፈለጉት አካባቢ ለመኖር የተጎናፀፉት የዜግነት መብታቸዉስ ለምን ይነጠቃል?*

## *4. የንብረት መብት*

*ምደረ ክርስቲያን በመላዉ ኢትዮጵያ ፋሲካን በአል እያከበረ ባለበት ሌሊት፤ ቅዳሴና ዝማሬ ለአምላኩ ለክርስቶስ እያቀረበ ባለበት የትንሳኤ በአል ፣ ፆሙን በደስታ እየፈሰከ ባለቤት ሌሊት የሰባት ተፈናቃይ አርሶ አደሮች ቤት በእሳት ሲጋይ ማደሩን መኢአድ ሰሞኑን ባወጣዉ መግለጫዉ ጠቅሶ ይህ ጉዳይም እንዲቆም አሳሰቦአል፡፡ ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች በበዓለ ፋሲካ ከቤታቸዉ ተፈናቅለዉ ባሉበት ሁኔታ ቤታቸዉና ንብረታቸዉ በእሳት ሲቃጠል ሌሎች ወገኖችም ወጥተዉ በመመልከታቸዉ ብቻ የእስር እንግልት እንደደረሰባቸዉም በመግለጫዉ ላይ ተብራርቶ ተገልፆአል፡፡*

*አዲስ አድማስ ፣ ሪፖርተር፣ ፍትህና እና ሌሎች ሚዲያዎች ደግሞ በጥልቀት እንደዘገቡትና ሰፋሪዎችም እንደገለፁላቸዉ ' ንብረታችሁን ያፈራችሁት እዚሁ ስለሆነ ንብረታችሁን ትታችሁ ዉጡ ተብሎ ተነግሮን ባዶ እጃችንን እንድንወጣ ተደርገናል፡፡ ሌሎቻችን ደግሞ በአጭር*

*ጊዜ ዉጡ ስንባል ንብረታችንን ቦታ ቦታ የምናሲዝበት ጊዜ ይሰጠን ብለን ስንጠይቅ ንብረታችሁን ከፈለጋችሁ ዋጡት ወይም ኢቃጥሉት የሚል መልስ ተሰጥቶን ከአካባቢዉ አንዲትም ንብረት ሳንይዝ እንድንወጣ ተደርገእ፡፡' ሲሉ ያብራራሉ፡፡*

*ሆኖም ህገ መንግስቱ የንብረትን ጥበቃ ጉዳይ በዝርዝር አስፍሮ ለዜጎችም ንብረት ከፍተኛ ጥበቃ ሊደረግለት እንደሚገባ በአንቀፅ **40** በስፋት ያብራራል፡-*

- *ማንኛዉም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል **(40/1)***
- *በጉልበት በካፒታል ወይም በፈጠራ ችሎታ የተገኘ ሀብት**(40/2 )**ሁሉ ንብረት ሲሆን የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ**(40/3)***
- *የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመነቀል መብታቸዉ የተከበረ ነዉ **(40/4)***
- *ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባዉ ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያርገዉ ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለዉ፡፡ ይህ መብት የመሸጥ የመለወጥ የማዉረስ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠዬቅ መብትን ያካትታለል**(40/7)***

*እንዲያዉም አንቀፅ **26/1** ይህን ጉዳይ ሲያብራራ ማንኛዉም ሰዉ የግል ህይወቱ የመከበር መብት አለዉ፡፡ ይህ መብት መኖርያ ቤቱ ሰዉነቱና ንብርቱን ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታዉ ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል ይላል፡፡*

*እንግዲህ በህገመንግስቱ መሰረት እነዚህ ዜጎች ግልፅ የሆነ የንብረት መብት አላቸዉ፡፡ ሆኖም ደቡብ ኢትዮጵያ ያፈራህዉን ሀብት እዚቸዉ ትተሃት ወደ አማራ ክልልህ ነቅለህ ጥፋልኝ የሚለዉ ሀሳቢ ህገ መንግስቱን መቃረን ወይም መናድ ነዉ፡፡ ደግሞም እንደ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር እነዚህ ሰዎች በዬትኛዉም ክልል መሬት በነፃ የማግኘትና ሀብት የማፈራት መብታቸዉ የተጠበቀ መሆኑን ህገ መንግስቱ በግልፅ ደንግጎአል (40/4)፡፡ ከላይም እንደ ጠቀስንዉ በይትኛዉም የኢትዮጵያ ክፍል ተዘዋዉረዉም መኖር ህገመንግስታዊ መብታቸዉ ነዉና በዬትኛዉም ክልል መርጠዉ መኖር ይችላሉ፡፡ ምናልባትም አንድ ሰዉ ወንጀል ቢሰራ፤ ጥፋት ቢያጠፋ ፍርድ ማግኘት ያለበት በፍርድ ቤቶች ነዉ እንጅ ከሚኖርበት አካባቢ ወይም ሊኖርበት ከመረጠዉ አካባቢ ይባረር የሚል ህግ የለም፡፡ ህጉ አስፈላጊዉን ቅጣት ሁሉ ጥፋቱን ባጠፋዉ ግለሰብ ላይ የሚወስደዉም በፍርድ ቤቶች ሲሆን በፍትሐብሄሩም ሆነ በወንጀል ህጉ ዉስጥ አንድ ዜጋ ጥፋት በማጥፋቱ ከአካባቢዉ ይባረር የሚል አንቀፅ የለም፡፡ ቢኖርም ቅሉ ህገ መንግስቱ የህጎች የበላይ ነዉና ገዥ ሆኖ የሚወጣዉ ህገመንግስቱ ዉስጥ ያለዉ ሀሳቤ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡*

## ***5. ህግ የማግኘት መብት***

*የአካባቢዉ ካድሬ/ፖሊስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንኳዋን ሳይይዝ በምን ስልጣኑ ነዉ ዜጎችን ከአንድ አካባቢ የሚያባርረዉ? ፍርድና ዉሳኔን የመስጠት ስልጣንስ አለዉ? ፍርድን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ሊሰጥ የሚችለዉ ፍርድ ቤት ሆኖ ሳለ እንዴት ዜጎች አለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በካድሬ ትዕዛዝ ብቻ ከሀገራቸዉ ይባረራሉ? ለመጭዉ ትዉልድስ ይህ ጥሩ የአስተሳሰብ ቅርስ ነዉ? እርግጥ ነዉ አንድ ወገን የጉልበት ብልጫ ካለዉ ሌላዉን ወገን ተነሳ ፤ተቀመጥ ፤ ተንቆራጥ እናም ተንከባለል ካሰኘዉም ተሰቀል ሊለዉ እና ያሰኘዉን ሊያደርገዉ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚከሰተዉ ግን የህግ መሰረትና ሀሳቤ የሰዎችን ስነባህሪና ድርጊት በማይገዛበትና በማይመራበት ሁኔታ ዉስጥ ብቻ ነዉ፡፡ ሕገ መንግስት ፅፉና ቀርፃ በምትንቀሳቀስ አገር ዉስጥ ግን የሰዎች ስነባህሪና ድርጊተ በህገ መንግስት ህጎች ከዚያም ሲያልፍ ከህገ መንግስቱ በሚፈልቁና በሚወጡ ዝርዝር ህጎች መሰረት መገዛት አለበት፡፡*

*ህገ መንግስቱ ስለ ነፃ ዳኝነት አካል / አንቀፅ **78/** እና የዳኝነት ስልጣን/ አንቀፅ **79/** በግልፅ አስቀምጦአል፡፡ በየትኛዉም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛዉም የመንግስት አካል ፤ከማንኛዉም ባለስልጣን ፤ እንዲሁም ከማንኛዉም ተፅዕኖ ነፃ ነዉ(አንፅ **79/**)፡፡ ለምሆኑ ክልሉ ዜጎችን ከሀገራቸዉ የማባረር ስራ ሲሰራ የትኛዉ ፍርድ ቤት ወስኖለት ነዉ?*

*ከዚህ በተጨማሪም አንቀፅ 37 ስለ ፍትህ የማግኘት መብት ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ (አንቀጽ 37/1 ) ብሎ ቢናገርም እነዚህ ተፈናቃይ ወገኖች ለተለያዩ ሚዲያዎች ብሶትና በደላቸዉን ያቀረቡት እንደሚከተለዉ ነዉ :- ፣ በወረዳም ፤ በዞንም፤ በክልልም ወዳሉ ፍርድ ቤቶች ሰንሄድና አቤት ሰንል ፍርድ ቤቶች ሊያስተናግዱን አለመፈለጋቸዉ አሳዝኖናል::' እና ታዲያ ህገ መንግስቱን ማን ይተግብረዉ? ፍርድ ቤት ፍርድ ለመስጠት ካልደፈረ በህገ መንግስት የተሰጠዉን ስልጣን በፖለቲከኞች ዉሳኔ ካስነጠቀ ታዲያ ፍርድ ቤቶችስ ህገ መንግስቱን በመናድ ተባበሩ ማለት አይደለም?*

*እንደሚታወቀዉ ዜጎች በጋራ የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ትፈጠር ዘንዳ መንግስት የብሄሮችን የብሄረሰቦችን የህዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነት አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት (አንቀፅ 88) እንጅ ይህኛዉ ከዚህኛዉ አካባቢ ያኛዉ ከዚኛዉ በማለት ወይም የዚህ አካባቢ ሀብት ለዚህኛዉ ብቻ በማለት ህጋዊ ስራዉን ዘንግቶ በህጋዊነት ያልተሰጠዉን ስራ መስራት የለበትም::*

*ወይም ሰሞኑን የደቡብ ክልለ ባለስልጣናት እያደረጉት እንዳሉት ከህገመንግስት ያፈነገጠ እርምጃ ከወሰዱ ብሁዋላ የተለያዩና ወጥነት የሌላቸዉን መግለጫዎችን መስጠት ህገ መንግስታዊ አካሄድ አያስብለዉም:: በሚዲያዎች ስለተባረረዉ ሰዉ ቁጥር የተለያዩ ቁጥር ይሰጣል:: የተባረረዉ ሰዉ ቁጥር ሰምንት መቶ ነዉ፤ አንዴ ደግሞ ሶስት ሽህ ነዉ :: ሌሎች ምንጮች ደግሞ ሀያ ሁለት ሽህ ወይም ሰባ ሰምንት ሽህ ነዉ የሚሉ መረጃዎች ሲኖሩ ክልሉ ግልፅ መረጃ ለኢትዮጵያ ህዝብ እስካሁን በማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ አልቻለም::*

*ዋናዉ ጥያቄ ግን አስርስ ሆነ አንድ ኢትዮጵያዊን የሚያባርሩት በምን የህግ መሰረት ነዉ ? የሚለዉ ነዉ:: መኢአድ በተለያዩ ወቅት በቢሮዉ እያስጠለለና ምግብ እየመገበ ወደ ሰሜን ሸዋ በብዙ አዉቶብስ መኪና የተሸኙት ወገኖች እንዲሁም በአአ የቀበሌ መጠለያዎች ዉስጥ በርካታ መቶ ሰዎች እንደተጠለሉ እየታወቀ የደቡብ ክልለ ለምን የተባረሩት አንዴ ሰላሳ ሶስት ናቸዉ አንዴ ደግሞ ሰምንት መቶ ናቸዉ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሶስት ሽህ ናቸዉ ወይም ደግሞ ሀያ ሁለት ሽህ ሰዎች ይባረራሉ በማለት እርስ በእርሱ የሚቃረን እና እዉነትን የማድበስበስ ስራ እንደሚሰራ ግልፅ አይደለም:: እዉን እንዲህ ያለ ስራ ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊ ወገኑ ላይ ሊፈፅመዉ ይቅርና ሲታሰብ እንኩዋን ለህሊና ምቾት ይሰጣል ?*

*ህገ መንግሰቱ ለሴቶች መብት ( አንቀ ፅ 35 ) እና ለህጻናት መብት (አንቀፅ 36) ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸዉ ቢገልፅም የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ እንዲሁም የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ እንደ ዘገቡት ህፃናት ከትምህርት ገበታቸዉ ላይ በጉልበትና በግዳጅ እየተፈናቀሉ፤ ለርሃብና ለጥማት እየተዳረጉ እናቶችም በመንገድ እየወለዱ የእንግዴ ልጃቸዉን ዉሻ እየበላዉ ይባስ ብሎም በሚያልፉበት አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች እንዳያስጠጉዋቸዉ መመሪያ እየተሰጠ በከፍተኛ መከራና ሰቃይ ዉስጥ እንዲያልፉ እየተዳረገ ነዉ::*

*ተፈናቃዮቹ እንደሚተርኩት ትምህርት ቤትና መንገዶችን ሰርተዉ በአካባቢዉ ባለስላጣናት እንዳስመረቁና ለዚህም ታታሪነታቸዉ የምስክር ወረት ሁሉ እንደተሰጣቸዉ ነዉ:: 'ሆኖም ዛሬ እኛ ባሰራንዉ ት/ቤት ልጆቻችን እንደይማሩበት ተከለከሉ::' ሲሉ ምሬታቸዉን ለተለያዩ ሚዲያዎች ገልፀዋል::*

*ዛሬ ሰዉ እንኩዋን በሀገሩ በኢትዮጵያ በሰዉ ሀገር ሄዶ ሀብት አፍርቶ ተከብሮና ታፍሮ ከሰዉ ልጆች ጋር ሁሉ በህብረትና በዉህደት በሚኖርበት ዘመን ዜጎች በኢትዮጵያ ሀብት በማፍራት ተፅዕኖን በአካባቢዉ ማህበረሰብ ላይ ፈጠራችሁ ፤ ዛፍ ጨፈጨፋችሁ ተብለዉ መባረራቸዉ አግባብ ነው ? ህገ መንግስቱስ የሚደግፈዉ እርምጃ ነወይ?*

## *6. ማካካሻ የማግኘት መብት*

በቅርቡ በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ዩኒቨርስቲዎችና ባለአዕምሮ ሊቃዉንት አስፍተዉና አጥልቀዉ እያራመዱት ያለዉ የህግ ትምህርትን ከኢኮኖሚክስ እንዲሁም የህግ ትምህርትን ከልማት ሳይንስ ጋር በማጋባትና በማዋሃድ የተዋጣለት የማህበረሰብ የእድገት ቀመር ፍሊጋና አሰሳን በመጠኑም ቢሆን ያነበበ ባለስልጣንና ፖሊሲ አዉጭ ስለልማት ሲያስብ ወይም ስለ ኢኮኖሚ ልማት ሲጨነቅ አብሮና አጣምሮ የሚያስበዉ ጉዳይ የህጉንም ዘርፍ ነዉ፡፡ ህግ በልማት ጉዞ ላይ ያለዉ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጫና ተሰፍሮና ተለክቶ አያልቅምና፡፡ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በፍጥነት በልማት የመራመድ ትልም ያለዉ ሀገር ከልማቱ ጋር የህጉን ቅንጅት አጥብቆና አጥልቆ ማስተሳሰር ካልቻለ የልማቱ ፍጥነት ፤ ቀጣነት ብሎም ምሉዕነት መሰናሰኛዉና ዉሉ ለተወሰኑ ግለሰቦች በዉፍረት የሚታይ ለቀሪዉ ደግሞ በብኸታና በቅጥነት የሚስተዋል ጉዳይ እንዳይሆን ተገቢ ትኩረት ለዘርፈ ብዙ ጉዳች መስጠት መልካም ነዉ፡፡

*ከሀገራቸዉ ከጉራፋርዳ የተፈናቀሉ ዜጎች ደጋግመዉ ሲናገሩ የሚደመጠዉ ከመሰረቱት መልካምና የተደላደለ ህይወት ወደ ድህነትና ወደ መጥፎ ህይወት እየተገፉ ያሉት ህጉ በልማት ጎዳና ላይ የሚያደርጉትን ግስጋሴ ሊያስከብርላቸዉ ስላልቻለ ነዉ፡፡ በተደላደለ ህይወት ዉስጥ ፤ ድህነትን አሸንፈዉ የተሻለ ዜጎች ለመሆን አፈር ገፍተዉ ደፋ ቀና ይሉ የነበሩ በርካታ ሽህ ዜጎችን ወደ አዘቅታዊ ድህነት መግፋት ህገ መንግስትቱን መናድ ነዉ፡፡ ልማት ማለት በሁሉም ዜጎች ርብርብ የሚመጣ እንጂ በጥቂት ኢንቨስተሮች የሚመጣ ጉዳይ አይደለም፡፡ በልማት ጎዳና እየገሰገሱ የነበሩ ዜጎችን ከልማት ማናጠብና ወደ ማይጨበጥ ድህነት መምራት ህገ መንግስቱን መጻረር ነዉ፡፡*

*ምናልባትም ቦታዉ ለልማት ተፈልጎ ከሆነም ዜጎች አላግባብ ልክ ዜጋ እናዳልሆኑ ሁሉ መብታቸዉ ሳይከበርና ካሳ ሳይሰጣቸዉ መባረር የለባቸዉም፡፡ በህገ መንግሰትቱ በአንቀፅ 44 / 2 አንደተብራራዉ መንግስት በሚያካሂዳቸዉ ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸዉ የተነካባቸዉ ሰዎች ሁሉ በመንግስት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡ ሆኖም ከቤንች ማጅ የተባረሩ ዜጎች ይህን እድል ሊያገኙት ይቅርና አቤቱታቸዉን በአግባቡ እህ ብሎ የሰማቸዉ ፍርድ ቤት የለም፡፡ በተለያዩ ሚዲያዎች እንደተዘገበዉና እነሱም እንዳብራሩት ፤- 'በአዉቶቡስ እየተጠረዝን በሌሊት ወደ ትዉልድ አገራችሁ እየተባልን እንባረራለን፡፡ አገራችን ከኢትዮጵያ ዉጭ ወዴት ነዉ? ህገመንግሰትቱ የሰጠንን በሁሉም ኢትዮጵያ የመኖር መብት የአካባቢ ባለስልጣኖች እንዳሰኛቸዉ የሚነጥቁን ከሆነ ዋስትናችን ምንድን ነዉ ? ፍርድ ቤቶችስ ምን አይነት ጫና ቢኖርባቸዉ ነዉ የእኛን ጉዳይ እንዳያዩ የወሰኑት?' እያሉ ተፈናቃዮቹ በርካታ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፡፡ ጥያቄዉ ግን ወደ ልቦና ባይገባም እንኩዋን ቢያንስ ጆሮ ላይ ነጥሮ ቢመለስም ቅሉ የሰዎቹን ጩሀት ያደመጣቸዉ የለም፡፡*

## *7.የተፈናቃዮች የፍትህ ጥያቄ*

*በተለያዩ ሚዲያዎች የተለያዩ ተፈናቃይ አርሶ አደሮች የፍትህ ጥቄያቸዉን በተለያዩ መልክ ሲያቀርቡ ተደምጠዋል፡፡ ሆኖም ሲጠቃለልና ሲጨመቅ ፡-'እኛ ገበሬዎች ነን፡፡ ሰርተን እና አፈር ገፍተን በሀገራችን በኢትዮጵያ መኖር ብቻ ነዉ የምንፈልገዉ፡፡ ጥቄያችንም የተነጠቅንዉ ህገ መንግስታዊ መብታችን ይከበር፤ ሀብታችን ይመለስ፤ ወደ ነበርንበት ቦታችንም እንመለስ፤ ቦታዉን መንግስት ለልማትም ከፈለገዉ ተመጣጣኝ ካሳ ይሰጠንና ሌላ ጋ ያስፍረን፤ እንዲሁም የተቃጠለዉ ቤታችን እና ንብረታችን ተገምቶና ተሰልቶ ካሳ ይሰጠን' የሚል መልዕክት ያለዉ ሆኖ ይገኛል፡፡*

*በህገ መንግስቱ መነፅር ጉዳዩን ስንመረምረዉ ደግሞ የተፈናቃዮቹ ሰዎች የአማራ ብሄር ወይም የሌላ ብሄር መሆናቸዉ ትርጉም የለዉም፡፡ ዋናዉ ነጥብና ጥያቄ ይህ አሁን በደቡብ ክልል የተወሰደዉ እርምጃ የዜጎችን በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የመኖር መብትን የሚነጥቅ ነዉይ? ይህ አስተሳሰብ እንደ እሴት ሆኖ በማህበረሰባችን ዉስጥ ከሰረፀ ዛሬ በእነዚህ ወገኖች የተጀመረ አካሄድ ወደ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት ላለመንደርደሩ ማረጋገጫ አለ ወይ? ኢትዮጵያዊ በሁሉም ቦታ እንዳይኖር የመከልከል አካሄድ ህገመንግስቱን ከመጣሱም በላይ ለመጭዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጥልቅ ነቀርሳን ፈጣሪ እሴት አይደለም ወይ ? **ስምሆኑስ የክልሉ መስተዳድር ዜጎችን ከክልሉ የማባረር ስልጣን አለዉ ወይ ? በዚህና መሰል ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች ሸሸትና ዝምታን መምረጥስ አግባብ ነዉይ? በኢትዮጵያ የህግ አስፈፃሚዉ፤ የህግ አዉጭዉና የህግ ተርጉዋሚዉ አካላት የስልጣን ክፍፍል፤ ሚዛን ጥበቃና የእርስ***

***በእርስ ቁጥጥር በዚህና በመሰል ጉዳዮች ላይ በመንተራስ ሲመረመር ተጎትቶ የሚወጣዉ እዉነት ምንድን ነዉ?***
*የሚሉት ጥቄዎች በልዩ ልዩ የህግ፤ የስነልቦና፤ የሶሽዎሎጂ ፤የኢኮኖሚክስ፤ የታሪክ፤ የፖለቲካ፤ የልማት ሳይንስ ወዘተ ምሁራን ትንታኔ እንዲቀርብባቸዉ ሀሳብ እያጫርኩ ለዛሬ ፅሁፌን እዚህ ላይ እገታለሁ፡፡*

*የጥበብና የፍቅር  አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን*

*ኢትዮጵያን እግዚአብሄር ይባርክ !*